ጉባዔ ዐሥራ ሦስት::

ይ.ካ.

ይበል ካህን::

ለከ እግዚኦ ገባሬ ኵሉ ለዘኢታስተርኢ አምላክ ንሰፍሕ ነፍሰነ::

ለና ለ አንድ ወገን ነው፤ ኀቤከ ሲል ነው ሁሉን ወደ ፈጠርክ ወደ ማትመረመር ወደ አንተ እደ ልቡናችንን እንዘረጋለን:: ለእመ ኢትክል ሰፊሐ እዴከ ስፍሖ ለኀሊናከ እንዲል::[130] አንድም በቁሙ ለማትታይ ሁሉን ለፈጠርክ ላንተ ሰውነታችንን እንደ ታጠበ ሸማ እንደ ተተከለ ትርሽማ አድርገን እናቀርባለን:: አንድም በአንቃዕድዎ ልቡና በሰፊሐ ኀሊና ለማትታይ ለአንተ ራሳችንን እናስገዛለን:: ለዘኢታስተርኢ አለ ምንም ሥጋዊውን ከንጉሡ እስከ ኳደሬው መንፈሳዊውን ከሊቀ ጳጳሱ እስከ አናጉንስጢሱ አድሮ የሚመግብ እሱ ቢሆንም አይታይምና::

ለከ ናቴሕት ዘአንተ መትሐቲ ለኵሉ::

ዘታቴሕት ኵሎ ሲል ነው ሁሉን ለምታዋርድ ላንተ እንዋረዳለን:: አንድም ሁሉ ለሚዋረድልህ ላንተ ራሳችንን እናዋርዳለን::

ወለከ ንሰግድ ዘአንተ መስገዲ ለኵሉ::

ዘታሰግድ ኵሎ ሲል ነው ሁሉን ለምታሰግድ ላንተ እንሰግዳለን:: አንድም ሁሉ ለሚሰግድልህ ለአንተ እንሰግዳለን::

ወለከ ንትቀነይ ዘአንተ መቅነዩ ለኵሉ::

ዘታቀኒ ኵሎ ሲል ነው ሁሉን ለምታስገዛ ላንተ እንገዛለን:: አንድም ሁሉም ለሚገዛልህ ለአንተ እንገዛለን::

---

[130] ሳትሞት ለባልንጀራህ በጎ ነገር አድርግ፤ እጅህንም ዘርግተህ የተቻለህን ያህል ስጥ:: ሲራክ ፲፬፡፲፫ ፤ እጅህን ልትዘረጋለት ባትችል እንኳን ኀሊናህን ዘርጋለት:: ዮሐንስ አፈ ወርቅ ተግሳጽ ፳፪

አ ሰጣሒሁ ለጎበኣ።

ይህን ዓለም እምነበ አልቦ ነበ ቦ ካለመኖር ወደ መኖር ካለመታየት ወደ መታየት አምጥጠህ የፈጠርኸው አንተ ነህና። አንድም የተሠወረውን የምትገልጥ አንተ ነህ።

ወከባቲሁ ለኵሉ ክሡት።

ኂላም ከመኖር ወደ አለመኖር ከመታየት ወደ አለመታየት የምታሳልፈው አንተ ነህ። አንድም የተገለጠውን የምትሠውር አንተ ነህ፤ አንድም አ ሰጣሒሁ ለጎበኣ ዲያብሎስን የምታዋርደው አንተ ነህ፤ ወከባቲሁ ለኵሉ ክሡት በዲያብሎስ ቦታ አዳምን የምታገባው አንተ ነህ። አንድም አ ሰጣሒሁ ለጎበኣ አዳምን የምታዋርደው አንተ ነህ፤ ወከባቲሁ ለኵሉ ክሡት አዳምን በንስሐ ወደ ቀደመ ክብሩ የምትመልሰው አንተነህ። አንድም አ ሰጣሒሁ ለጎበኣ ባሕርየ መለኮትን በሥጋ የምትገልጠው አንተ ነህ፤ ወከባቲሁ ለኵሉ ክሡት ሥጋን በመለኮት በርቀት የምትሠውረው አንተ ነህ። አንድም አ ሰጣሒሁ ለጎበኣ ሥጋህን ደምህን በስንዴ በወይን የምትገልጠው አንተ ነህ፤ ወከባቲሁ ለኵሉ ክሡት በመለወጥ የምታጸናው አንተ ነህ። አንድም አ ሰጣሒሁ ለጎበኣ ኃጢኣተ አይሁድን በጽሕፈት የምትገልጠው አንተ ነህ፤ ወከባቲሁ ለኵሉ ክሡት የአንዱን ኃጢኣት አንዱ እንዳያውቀው የምታደርግ አንተ ነህ፤ ወከደንከ ኵሎ አበሳሆሙ እንዲል። አንድም አ ሰጣሒሁ ለጎበኣ ኃጢኣተ አይሁድ የምትገልጠው አንተ ነህ። ወከባቲሁ ለኵሉ ክሡት ኃጢኣተ ዘማን የምትሠውር አንተ ነህ። ጌታችንም ወደ ደብረ ዘይት ሄዶ በጠዋት ከምኩራብ ገብቶ በዚያ የተሰበሰቡትን ያስተምራቸው ጀመር ጸሐፍት ፈሪሳውያን በዝሙት የተገኘች ሴት ወደ እርሱ አመጧት ወደ ውስጥም አግብተው አቆሟት፤ መምህር! ይህች ሴት በዝሙት ስትበድል አገኘናት በሕጋችን ሙሴ በዝሙት የተገኘች ሴት በድንጋይ ተወግራ እንድትሞት አዟል አንተ ስለ እርሷ ምን ትላለህ? አሉት። ጌታችንም ወደ ምድር ተመለከተና በጣቱ ጻፈ ዐይኖቹንም አንሥቶ ከእናንተ መካከል ኃጢኣት የሌለበት አስቀድሞ ይውገራት አላቸው እነሱም ይህን ተግሣጽ በሰሙ ጊዜ ኃጢኣታቸውን አስበው ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ መጨረሻ አንድ አንዳንድ እያሉ ጥለው ወጡ ያችም ሴት ከወለሉ ላይ ብቻዋን ቀረች፤ ጌታችንም ቀና ብሎ ወደ እርሷ ተመለከተና አንቺ ሴት! የሚከሱሽ

ወዴት አሉ? አላት፤ እሷም ጌታዬ! የማየው የለም አለችው እኔም አልፈርድብሽም ወደ ቤትሽ ሂጂ ዳግመኛ እንዳትበድዪ አላት።

ኦ አውሳኢሁ ለዘእንተ ውስጥ።

ዲያብሎስን የምታዋርደው አንተ ነህ። ወአባኢሁ ለዘእንተ አፍአ በዲያብሎስ ቦታ አዳምን የምታገባው አንተ ነህ። አንድም ኦ አውሳኢሁ ለዘእንተ ውስጥ አዳምን የምታዋርደው አንተ ነህ፤ ወአባኢሁ ለዘእንተ አፍአ በንስሐ የምትመልሰው አንተ ነህ። አንድም ኦ አውሳኢሁ ለዘእንተ ውስጥ ጴጥሮስን የምታዋርደው አንተ ነህ፤ ወአባኢሁ ለዘእንተ አፍአ ኂላም በንስሐ የምትመልሰው አንተ ነህ። አንድም ኦ አውሳኢሁ ለዘእንተ ውስጥ ይሁዳን የምታዋርደው አንተ ነህ ወአባኢሁ ለዘእንተ አፍአ በይሁዳ ቦታ ማትያስን የምታገባው አንተ ነህ። አንድም ኦ አውሳኢሁ ለዘእንተ ውስጥ ጸሐፍት ፈሪሳውያንን የምታወጣ አንተ ነህ፤ ወአባኢሁ ለዘእንተ አፍአ በጸሐፍት ፈሪሳውያን ቦታ ሐዋርያትን የምታስገባ አንተ ነህ። አንድም ኦ ሰጣሒሁ ለኀቡእ በውስጥ የነበረ ከአርባ ሐራ ሰማይ አንዱን የምታወጣው አንተ ነህ፤ ለሉሲ ክሡት በአፍአ ከነበሩ ከአሕዛብ አንዱን የምታገባው አንተ ነህ፤ ይህስ እንደምንድን ነው ቢሉ አንድ አላዊ ንጉሥ አርባ ሐራ ሰማይን እንደ ሰይፍ ከሚቆራርጥ እንደ መቀስ ከሚከፋፍል ቀዝቃዛ ባሕር ውስጥ አስገባቸው፤ አርባ ቀን ሲሆናቸው መላእክት አርባ አክሊላትን ይዘው ረበው ታዩ ከእነዚያ አንዱም መከራውን ተሰቅቆ አውጡኝ አውጡኝ አለ አወጡት ወዲያው ነፍሱ ከሥጋው ተለየች ሠላሳ ዘጠኙ አክሊላቱን ተቀብለው አንዲቱ አክሊል ግን ተንጠልጥላ ቀረች ከአሕዛብ አንዱ አምኖ በሰማዕትነት ሞቶ ተቀብሎታልና እንዲህ አለ።

ወይእዜኒ ስማዕ አውያቶሙ ለሕዝብከ ወለእለ ይጼውዑከ በጽድቅ።

ስማዕ በጽድቅ ይጼውዑከ በጽድቅ ነው በእውነት የሚለምኑህን ልመናቸውን በእውነት ስማቸው በሐሰት ሆኖ ቢለምኑት አይሰማምና።

ይዳ. ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት።

ዲያቆን ለእግዚአብሔር በረዓድ በፍርሃት ስገዱ ይበል።

ይሐ. ቅድሜከ እግዚኦ ንሰግድ ወንሴብሐከ።

ሕዝቡም አቤቱ በፊትህ እንሰግዳለን እናመሰግንሃለን ይበሉ።

Scanned by CamScanner

ይ.ካ. ጸሎተ ንስሐ፡፡

ይ.ዲ. ነጽር፡፡

ዲያቆኑ ሥጋው ደሙ እንዳይነጥብ ተሐዋስያን እንዳይቀርቡ ተመልከት ይበል፤ አንድም የበቃውንና ያልበቃውን ተመልከት ግብር ገብተህ አስተውል፤ አንድም ሳይጠብቅ ነጽር ይላል ግብር ገብተህ የበቃውንና ያልበቃውን ለይ፡፡

ይ.ካ.

ይበል ካህን፡፡

ቅድሳት ለቅዱሳት፡፡

ሥጋው ደሙ ለበቃ ነው በቅቶ ይቀበል እንጂ እኔ ስንቱ እለየዋለሁ ይላል አንድ መነኩሴ በጾም በጸሎት በስግደት በትሕርምት አርባ ዘመን በበረሃ ወድቆ ይኖር ነበር፤ መልአኩ ሥጋ ወደሙ ካልተቀበልክ ገድልህ ትሩፋትህ ምን ይረባሃል ምን ይጠቅምሃል ሥጋ ወደሙ ከሚፈተትበት ሄደህ ተቀበል አለው ያም መነኩሴ ሥጋውን ደሙን ሊቀበል ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደ፤ ሲያስቀድስ ካህኑ ቅድሳት ለቅዱሳት ሥጋ ደሙ ለበቃ ነው እንጂ ላልበቃ አይደለም ሲል ሰምቶ ሰማይኒ ኢኮነ ንጹሐ በቅድሜየ መኑ ሰብእ ዘይነጽሕ[131] ይላል በቅቻለሁ ብዬ ብቀበልማ ዕዳ ይሆንብኝ የለምን ብሎ አልበቃሁም ብሎ ተመልሶ ሄዷል ሁለተኛ መጣ ይህን ሲባባሉ ሰምቶ አልበቃሁም ብሎ ተመልሶ ሄዷል ሦስተኛ መጣ ይህን ሲባባሉ ሰምቶ አልበቃሁም ብሎ ተመልሶ ሲሄድ መልአኩ አንተስ በቅተሃል ተቀበል ብሎት ተቀብሏል፡፡

ይ.ሕ.

ይበሉ ሕዝብ

አሐዱ አብ ቅዱስ፡፡

በባሕርይ በህልውና ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አንድ የሚሆን አብ ንጹሕ ነው ካልነጹ አያድርምና፡፡

---

131 ሕያው ሁሉ በፊትህ ጻድቅ አይደለም፡፡ መዝሙር ፻፵፪ ፥ ፪ ፤ ሰማያትም በፊትህ ንጹሐን አይደሉም፡፡ ኢዮብ ፲፭ ፥ ፲፭

አሐዱ ወልድ ቅዱስ፡፡

በባሕርይ በህልውና ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አንድ የሚሆን ወልድ ንጹሕ ነው ካልነጹ አያድርምና፡፡

አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ፡፡

በባሕርይ በህልውና ከአብ ከወልድ ጋራ አንድ የሚሆን መንፈስ ቅዱስ ንጹሕ ነው ካልነጹ አያድርምና፡፡

ይ.ካ. እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ፡፡

ካህኑም እግዚአብሔር በሁላችሁም አድሮባችሁ ይኑር ይበል፡፡ አንድም በረድኤት በጸጋ ከሁላችሁም ጋር ይሁን፡፡

ይ.ሕ. ምስለ መንፈስከ፡፡

ሕዝቡም እንደ ቃልህ ይደረግልን፡፡ ወብነ አሐዱ መንፈስ ዘሃይማኖት እንዲል፡፡ አንድም ቢመርቃቸው ይመርቁታል ብሎ ካንተ ጋራ ይደረግልን፡፡

ይ.ካ. እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ፡፡

አቤቱ ክርስቶስ ሆይ ማረን፤ እዘንልን ይቅር በለን ይበል፡፡

የቄሱ ፲፰ የሕዝቡ ፲፰፡፡ ፴፮ ይሆናል፡፡ ከዚህ በኋላ ቄሱ ፫ ጊዜ ሕዝቡ ፪ ጊዜ ፵፩ ይሆናል፡፡ እግዚኦታ የገባው በግርፋት ነው አንድ ተረፈሳ ቢሉ የአዳም ቀኖና ምሳሌ ታሪክ በገጽ ፶፩ /51/ ይመልከቱ፡፡

አንድም ኦሪት አርባ ግረፍ ከአርባ አትለፍ ትላለች ከአርባ የበዛ እንደሆነ አንተ አሕሰርካሁ ለእኁከ ትላለች ጌታን ግን ሠላሳ ዘጠኝ ገርፈውት ተሳሳትን ያሉ ስድስት ሺ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ጊዜ ገርፈውታል ሥጋ አልቆ አጥንቶ በረዶ እስኪመስል እንደ ብልጭት ነጥቶ እስኪወጣ ድረስ፤ አንድ ሁለት ተብሎ እስኪቆጠር ገርፈውታል፡፡

ይ.ዲ. እለ ውስተ ንስሐ ሀለውክሙ፡፡

በደልን ተመለስን በማለት ያላችሁ ርእሰ ልቡናችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ አንድም ልቡናችሁን ከትዕቢት አዋርዱ ይበል የልቡና ነው፡፡

ይ.ካ.

ይበል ካህን፡፡

እግዚአብሔር አምላክነ ነጽር ዲበ እለ ውስተ ንስሐ ሀለዉ።

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ሆይ በደልን ተመለስን ብለው በንስሐ ሕይወት ያሉትን በዐይነ ምሕረት ተመልከት አንድም ጠብቅ ይበል።

ወተሠሃሎሙ በከመ ዕበየ ሣህልከ።

እንደ ይቅርታህ ብዛት ይቅር በላቸው

ወበከመ ብዝኃ ምሕረትከ ደምስስ አበሳሆሙ።

እንደ ቸርነትህ ብዛት ኃጢአታቸውን አስተሥርይላቸው

ክድኖሙ።

በረድኤት ጠብቃቸው

ወዕቀቦሙ እምኵሉ እኩይ።

ከክፉ ነገር አጽንተህ ጠብቃቸው።

ወቤዙ ነፍሳቲሆሙ በሰላም አሕጸረከ ዘቀዳሚ ምግባሮሙ።

የቀደመ ኀጢአታቸውን ይቅር ብለህ በቅዱስ ሥጋህ በክቡር ደምህ አድናቸው። ይህ ይገኝበታልና ሰላም አለው አንድም የቀደመ ኃጢአታቸውን ይቅር ብለህ፤

ደምሮሙ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት።

ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲገቡ አድርጋቸው፤አንድም ከምእመናን አንድ አድርጋቸው

በሞገሱ ወበምሕረቱ ለዋሕድ ወልድከ እግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

ተቀዳሚ ተክታይ የሌለው ልጅህ ጌታችን ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይቅር በማለቱ በቸርነቱ።

ይዳ. ተንሥኡ ለጸሎት።

ዲያቆኑ ለጸሎት ተነሡ ይበል።

ይሕ. እግዚኦ ተማህለነ።

አቤቱ ይቅር ይበለን።

ይካ.

ይበል ካህን።

ሥጋ ቅዱስ ዘበአማን ዝ ውእቱ እማሬ ዘእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ::

በእውነት ንጹሕ ክቡር የሚሆን የክርስቶስ ሥጋ ይህ ነው:: አንድም ይህ የክርስቶስ ሥጋ በእውነት ንጹሕ ክቡር ነው::

ዘይትወሀብ ለሕይወት ወለመድኃኒት ወለሥርየተ ኃጢአት ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ በአሚን::

አምነው ለሚቀበሉት የኃጢአት ማስተሥርያ፣ ሕይወተ ሥጋ ሕይወተ ነፍስን የሚሰጥ መድኃኒት ነው::

ይ.ሕ. አሜን::

በእውነት የክርስቶስ ሥጋ ነው:: አንድም ንጹሕ ክቡር መሆኑ እውነት ነው:: አንድም አምነው ለሚቀበሉት ኃጢአትን የሚያስተሠርይ፣ ሕይወተ ሥጋ ሕይወተ ነፍስን የሚሰጥ መድኃኒት መሆኑ እውነት ነው::

ደም ክቡር ዘበአማን ዝ ውእቱ (እማሬ) ዘእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ::

ንጹሕ ክቡር የሚሆን እውነተኛ የክርስቶስ ደም ይህ ነው:: አንድም ይህ የክርስቶስ ደም በውነት ንጹሕ ክቡር ነው::

ዘይትወሀብ ለሕይወት ወለመድኃኒት ወለሥርየተ ኃጢአት ለእለ ይትሜጠዉ እምኔሁ በአሚን::

አምነው ለሚቀበሉት የኃጢአት ማስተሥርያ መድኃኒተ ሥጋ መድኃኒተ ነፍስ ሊሆን የሚሰጥ ክቡር ደም ነው::

ይ.ሕ. አሜን::

በእውነት የክርስቶስ ደም ንጹሕ ክቡር መሆኑ እውነት ነው፤ አንድም የክርስቶስ ደም ኃጢአትን የሚያስተሠርይ የነፍስና የሥጋ መድኃኒት መሆኑ እውነት ነው ይበሉ::

ይ.ካ. እስመ ዝንቱ ውእቱ (እማሬ) ሥጋሁ ወደሙ ለአማኑኤል አምላክነ ዘበአማን::

የፈጣሪያችን የአማኑኤል ሥጋው ደሙ ይህ ነው:: አማኑኤል ማለት አምላክ ወሰብእ ማለት ነው:: ወዝንቱ ስም ዐቢይ ጥቀ ዘኢይክሉ ፈሊጦቶ እንዲል:: አንድም አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ምስሌነ ማለት ነው:: ከእዚያ እየራሱ የተናገረውን ከእዚህ ደርቦ ተናገረው::

እየራሱ መናገሩ እየራሱ እንደተሰጠ ለማጠየቅ። ከዚህ ደርበ መናገሩ ሥጋው ከደሙ ደሙ ከሥጋው አንድ እንደሆነ። አንድም ሥጋውን ከደሙ ደሙን ከሥጋው አንድ እንዳደረገው ለማጠየቅ።

ይሕ. አሜን።

በእውነት የአማኑኤል ቅዱስ ሥጋው ክቡር ደሙ ነው።

ይካ. አአምን አአምን አአምን ወእትአመን እስከ ደኃሪት እስትንፋስ።

በውስጥ በአፍአ በነፍስ በሥጋ እስከ ዕለተ ሞት አንድም እስከ ምጽአት ድረስ አምናለሁ። አአምን አአምን አአምን የሦስትነት ወእትአመን የአንድነት ምሳሌ።

ከመ ዝንቱ ውእቱ (እማሬ) ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘነሥአ እምእግዝእተ ኩልነ ቅድስት ድንግል በክልኤ ማርያም።

ንዕድ ክብርት በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከእመቤታችን የነሣው የጌታ ሥጋው ደሙ እንደሆነ አምናለሁ።

ወረሰዮ አሐተ ምስለ መለኮቱ።

ከባሕርየ መለኮቱ ጋራ አንድ ያደረገው፤

ዘእንበለ ቱስሕት ወኢትድምርት።

ያለ መቀላቀል እንደ ውኃና ወተት ያለመጣፋት።

ወኢውላጤ።

ያለመለወጥ እንደ ብእሲተ ሎጥ እንደ በትረ ሙሴ እንደ ማየ ቃና፤

ዘእንበለ ፍልጥ።

ያለመለየት አንድ ያደረገው።

ወኮነ ለማዕተ በስምዕ ሠናይ በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ።

በጳንጦስ ሰው በጲላጦስ ፊት ያለመበሳጨት አንተኑ ንጉሠ አይሁድ ቢለው እስመ አነ በእንተ ዝንቱ መጻእኩ ወበእንተ ዝንቱ ተወለድኩ ከመ እኩን ለማዕተ በጽድቅ ብሎ የመሰከረ።

Scanned by CamScanner

ወመጠወ በእንቲአነ ወበእንተ ሕይወተ ኵልነ፡፡

ስለኛ ለሕማም ለሞት አሳልፎ የሰጠው የጌታ ሥጋ እንደሆነ፡፡ አንድም ለነ ሲል ነው ሁሉን ለማዳን ለእኛ ሕይወት መድኃኒት አድርጎ የሰጠን የጌታ ሥጋው ደሙ እንደ ሆነ አምናለሁ፡፡

ይ.ሕ. አሜን፡፡

አምላክ ሰው፤ ሰው አምላክ መሆኑ እውነት ነው ይበሉ፡፡

ይ.ካ.. አአምን አአምን አአምን ወእትአመን

ትርጓሜው እንዳለፈው ነው፡፡

ከመ ኢተፈልጠ መለኮቱ እምትስብእቱ፡፡

መለኮቱ ከትስብእቱ፤ ትስብእቱ ከመለኮቱ እንዳልተለየ፤

ኢአሐተ ሰዓተ ወኢከመ ቅጽበተ ዐይን፡፡

አንዲት ሰዓት ስንኳ ዓይን ከድኖ እስኪገልጡ፡፡ ስለሁላችን ቤዛ መድኃኒት አድርጎ ለሕማም ለሞት አሳልፎ ሰጠው እንጂ፡፡ አንድም ለኛ ሕይወተ ሥጋ ሕይወተ ነፍስ መድኃኒተ ሥጋ መድኃኒተ ነፍስ አድርጎ ሰጠው እንጂ፡፡

ወለሥርየተ ኃጢአት ለእለ ይትመጠዉ እምኔሁ በአሚን፡፡

አምነው ለሚቀበሉት የኃጢአት ማስተሥርያ ሊሆን ቤዛ አድርጎ ሰጠን እንጂ፡፡

ይ.ሕ. አሜን፡፡

ይ.ካ. አአምን አአምን አአምን ወእትአመን፡፤

ትርጓሜው እንዳለፈው ነው፡፡

ከመ ዝንቱ ውእቱ (እማሬ) ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡

የጌታችን የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው ደሙ እንደሆነ አምናለሁ፡፡

ዝ ውእቱ ዘሎቱ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወስግደት፡፡

ክብር የክብር ክብር ሰጊድ ገንዘቡ የሚሆን፡፡

ምስለ አቡሁ ኄር ሰማያዊ።

ልዑል ቸር ከሚሆን ከባሕርይ አባቱ።

ወመንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ።

ማሕየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስግደት የሚገባው የጌታ ሥጋው ደሙ እንደሆነ አምናለሁ።

ዘለሙቱ ይደሉ ክብር ወስብሐት።

ወስግደት ሲል በዝየ ይስግዱ ካህናት ወዲያቆናት ወይስዐሙ ይላል እጅ ይንሡ ማለት ነው። መስገዳቸው ለጌታ ነው ቅዱሳት አንስት ከመቃብር ደርሰው ሲመለሱ ጌታ ወተራከቦን እግዚእ ኢየሱስ በፍኖት ይላል ከጎዳና ተገናኝቶ እንዴት ሰነበታችሁ ባላቸው ጊዜ አታዛ እገሪሁ ወድቃ ወሰገዳ ሎቱ ይላል ከእግሩ ወድቀው ሰግደውለታልና የዚያ ምሳሌ ነው።

ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

ትርጓሜው እንዳለፈው።

ወእምዝ ይንሣዕ ካህን በእደሁ።

አስበ ዲያቆን ዘቦቱ ትእምርተ መስቀል ወይደዮ ውስተ ጽዋዕ ወይጥማዕ ቦቱ ደመ ወይን ሥጋ በትእምርተ መስቀል።

መጽሐፉ አአምንን አስቀድሞ ቡራኬውን በኂላ አድርጎታል ሥጋውን አአምን ደሙን ቡሩክ እያሉ ባርኪል ከዚህ በኂላ ካህን ትእምርተ መስቀል ያለበት አስበ ዲያቆኑን አንሥቶ በሥጋው ደሙን ጠምቶ ሥጋውን አመሳቅሎ ይባርክ።

ቅድመ ዲበ ክፍል ዘዐቢይ እንተ አፍአሁ።

አስቀድሞ በአፍአ ያለው ዐቢይን ክፍል።

ወዳግመ እንተ ውስቴታ።

ዳግመኛ የውስጡን ክፍል።

ወሣልስ ዲበ ክፍል ንዑስ።

ሦስተኛ ንዑሱን ክፍል ይባርክ።

Scanned by CamScanner

ወካዕበ ይዕትብ በሥጋ ደመ እንዘ ይብል ቡሩክ እግዚአብሔር እስከ ተፈጸሜቱ።

ዳግመኛም በሥጋው ደሙን ቡሩክ እያለ እስከ መጨረሻ ባርኮ፤

ይደዮ ውስተ ጽዋዕ ነው።

ሥጋውን በዐስበ ዲያቆኑ ደሙን ጠምቆ አአምን አአምን አአምን ብሎ ሦስት ጊዜ ይባርካል። ደሙን በሥጋው ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ዓለም አምላክነ ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጸራቅሊጦስ መጽንዔ ወመገሥጽሔ ኵልነ ብሎ ሦስት ጊዜ ባርኮ አስበ ዲያቆኑን ከጽዋው ውስጥ ያገባዋል። ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ፍጻሜ ጸሎት ነው። አንድም የፊሊጥ ቡራኬ በአስበ ዲያቆኑ ደሙን ጠምቶ አአምን ብሎ ሥጋውን ይባርካል። እንደያዘ ሳይጠማ ደሙን ቡሩክ ብሎ ይባርካል። ዳግመኛ ጠምቶ አአምን ብሎ ሥጋውን ይባርካል። እንደያዘ ቡሩክ ብሎ ደሙን ይባርካል። ሦስተኛ ጠምቶ አአምን ብሎ ሥጋውን ይባርካል። ባርኮ ሲፈጽም አስበ ዲያቆኑ ከጽዋው ያገባዋል። አስበ ዲያቆኑን በሀገራችን ዲያቆን ይቀበለዋል የእስጢፋኖስ ምሳሌ ነው ከጌታ ቀጥሎ ከሐዋርያት አስቀድሞ መከራ ለመቀበሉ ምሳሌ ነውና። በሮም ግን የጌታን መከራ መቀበል ይገባኛል ሲል ቁሱ ይቀበለዋል።

ወያምጽእ ንፍቅ ዲያቆን ማየ ለካህናት።

ንፍቅ ዲያቆን ውኃውን ለካህናት ያምጣ።

ወይትሐጸቡ እደዊሆሙ አምሳለ ቅዱሳን ነፍሶሙ።

ካህናት ንጹሓን እንደ መሆናቸው እጃቸውን ይታጠቡ። ለጊዜው ጻሕል ጽዋ የሚይዙ ናቸውና ፍጻሜው ግን እኛ ከአወቅነው ኃጢአት ነጽተናል እኛ ካለወቅነው ኃጢአት አንተ አንጻን ለማለት። አንድም በነፍሳቸው ንጹሓን እንደሆኑ ለማጠየቅ።

ወእምዝ ይበል ዘንተ ጸሎተ።

ይህ ሲናገር ለመጣው ነው ከዚህ በኋላ ይህን ይጸልይ።

እንዘ ይብል እግዚአብሔር አምላኪየ ናሁ ሥጋ ወልድከ መሥዋዕት ዘያሠምረከ።

ፈጣሪዬ እግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝህ መሥዋዕት የልጅህ ሥጋ እነሆ፤ እያለ ይጸልይ። ወአንከረ አብ እምዝንቱ መሥዋዕት እንዲል።

Scanned by CamScanner

ወበዝንቱ አናሕሲ ሊተ ዙሎ ኃጢአትየ።

በዚህ መሥዋዕት ኃጢአቴን ይቅር በለኝ።

እስመ በእንቲአየ ሞተ ወልድከ ዋሕድ።

ሥቃዳሚ ተከታይ የሌለው ልጅህ ስለኔ ኃጢአቴን ለማስተሥረይ አንድም እኔን ለማዳን ሞቷልና።

ወናሁ ደመ መሢሀክ ንጹሕ ዘተክዕወ በእንቲአየ በቀራንዮ።

ንጹሕ የሚሆን የልጅህ ደም እኔን ለማዳን ኃጢአቴን ለማስተሥረይ በቀራንዮ የፈሰሰ።

ይኬልሕ ሀየንቴየ።

ስለኔ ይካሰስልኛል። የተካሰሰ ዋጋ እንዲያሰጥ ዋጋዬን ይሰጠኛል። ለቅዱስ ሚካኤል እንደ ነገረው በሲኦል በገሃነመ እሳት ያሉትን ነፍሳት አይቶ ሄዶ ማራቸው ብሎ ተማፀነ።

አንተኑ ትምሕሮመ እምኔየ እምዘፈጠርክምዎመ ለነ።

ከፈጠርኋቸው ከኔ አንተ ታዝንላቸዋለህን። አንተስ ትስእል በእንቲአሆመ ለአሐቲ ሰዓት ወደምየሰ ይኬልሕ በእንቲአሆመ እስከ ለዝሉፉ አንተ ግን ስለእነሱ ለአንድ ሰዓት ትለምናለህ የእኔ ደም ግን እስከ ዓለም ፍጻሜ ሲፈስ ይኖራል ብሎ ነግሮታል።

ዝንቱ ደም ነባቢ ይኩን ሠራዬ ኃጢአትየ ለገብርከ።

ነባቢ የሚሆን ይህ ደም የኔን ያገልጋይህን የባሪያህን ኃጢአቴን የሚያስተሠርይልኝ ይሁን። ነባቢ አለው አስተሥራዬ ሲል ነው፤አጣሊሰ ኢይትናገር አላ ዘዚአነ ይትናገር እንዲል። አንድም ከኃጢአት ነጽቶ ቢቀበሉት በልሳነ ነፍስ ያናገራልና። ወሶበ ይበውእ ውስተ ልበ ንጹሕ አሜሃ ያነቅሖ ለተናግሮ እንዲል።

ወተወከፍ ስእለትየ በእንቲአሁ።

ስለወልድ አንድም ስለደመ ልመናዬን ተቀበልልኝ።

እስመ በእንቲአየ ኮናት ወቅንዋተ ተወክፈ ፍቁርከ።

ልጅህ ወዳጅህ እኔን ለማዳን በጦር መወጋትን በቀኖት መቸንከርን ተቀብሏልና።

Scanned by CamScanner

ወሐመ ከመ ያሥምርክ።

ፈቃድህን ይፈጽም ዘንድ መከራ ተቀብሏልና።

ወእምድኅረ ድኅንክ።

ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ ከሳሰልኝ በኋላ አንድም በጥምቀት በንስሐ ከኃጢአት ከፍዳ ከዳንሁ በኋላ።

ገብአ ሰይጣን ውስተ ልብየ ወነደፈኒ በአሕጻሁ።

ሰይጣን በልቡናዬ አድሮ ተዋጋኝ አንድም አሳተኝ

ሀበኒ እግዚኦ ምሕረትክ።

አቤቱ በቸርነትህ ድል መንሣትን ስጠኝ።

እስመ መስተዋቅስ ጽኑዕ ውእቱ።

ጽኑ ባላጋራ ነውና አንድም ወቃሽ ከሳሽ ነውና።

ወበስንቀ ኃጢአት ቀተለኒ።

ኃጢአቴን ተከትሎ። አንድም ኃጢአቴን ምክንያት አደርጎ ጎድቶኛልና።

ተበቀል ሊተ እምደፋሪ ዘኢይፀግብ አስሕቶትየ እምሕይወትየ።

ይፍልጠኒ ያለበት ነው ከዐቂበ ሕግ ይለየኝ ዘንድ አንድም ከሕይወቴ ካንተ ይለየኝ ዘንድ እኔን ከማሳት የማይሰለች። አንድም ኃጢአት ከመሥራት ሰውን ከማሳት በቃኝ የማይል ሰይጣንን አጥፋልኝ። አንድም ከሰይጣን አድነኝ።

አንተ ውእቱ እግዚኦ ንጉሥየ ወአምላኪየ ወመድኃንየ።

ፈጣሪዬ ገሸርዬ መድኃኒቴ አንተ ነህና።

አጽምም ቀሰለ ነፍስየ ወሥጋየ ለገብርክ።

በነፍስ በሥጋ ከሠራሁት ኃጢአት አንጻኝ ይበል።

ወእምቅድመ ተመጥኖ ቍርባን ይበሉ ዅሎሙ እለ ይነሥኡ እምሥጢር ቅዱስ።

ሥጋውን ደሙን ከመቀበል አስቀድሞ ሥጋውን ደሙን የሚቀበሉ ምእመናን ሁሉ ይህን ይድገሙ ይህ የሁሉ ጸሎት ነው።

Scanned by CamScanner

ኦ እግዚአየ ኢየሱስ ክርስቶስ አኮ ዘይደልወኒ ትባእ ታሕተ ጠፈረ ቤትየ ርኩስት::

አቤቱ ፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ጥፋር ቤትየ ሲል ነው:: በኃጢአት በተታታ (በተተበተበ) ሰውነቱ ማደር የሚገባህ አይደለም:: ሰብእናየ ታሕተ ማዕሰ ሲኑይ ከመ ደመና ዘጠፈረ ሰማይ እንዲል::

እስመ አነ አስተቄጣዕኩከ::

አሳዝኜሃለሁና::

ወገበርኩ እኩየ በቅድሜከ::

በፊትህ ክፉ ሥራ ሠርቻለሁና::

ወአርኰስኩ ነፍስየ ወሥጋየ ዘፈጠርከ በአርአያከ ወበአምሳሊከ በዐሊወ ትእዛዝከ::

ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ብለህ የፈጠርኸው ሰውነቴን በኃጢአት አሳድፌያለሁ ሕግህን በማፍረስ:: አንድም ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ብለህ የፈጠርኸኝ አንተን የማይገባ ሥራ ሠርቼ አስነቅፌሃለሁና::

ወአልብየ ምግባረ ሠናይ ወኢምንትኒ::

በጎ ሥራ የለኝም ዮነልዮ ስንኳ::

ወባሕቱ በእንተ ተኬንዎትከ::

ነገር ግን ስለ ፈጠርኸኝ::

ወበእንተ መስቀልከ ክቡር::

ስለ ተሰቀልህ፤ አንድም ስለ መስቀልህ፤

ወበእንተ ሞትከ ማሕየዊት::

ስለ ሞትህ፤

ወበእንተ ትንሣኤከ በሣልስት ዕለት::

በሦስተኛው ቀን ስለተነሣህ::

እስእለከ ወአስተበቁዐከ ኦ እግዚአየ ከመ ታንጽሐኒ እምኵሉ ኃጢአት ወርኵስ::

አቤቱ ከኃጢአት ከመርገም ከክህደት ታድነኝ ታነጻኝ ዘንድ አድነኝ አንጻኝ ብዬ እለምንሃለሁ እማልድሃለሁ፤ አንድም እለምንሃለሁ እንጂ በጎ ሥራ የለኝም ዮነልዮ ስንኳ::

Scanned by CamScanner

ወሶበ እትሜጥው ለምሥጢረ ቅድሳቲከ።

ሥጋህን ደምህን በተቀበልሁ ጊዜ።

ኢይኩነኒ ለትሥፈት ወኢለዕኑነኒ።

መወቀሻ መከሰሻ መፋረጃ አታድርግብኝ አንድም ለወቀሳ ለከሰሳ አይሁንብኝ የሚያስፈርድብኝም አይሁን።

አላ መሐረኒ ወተሣሃለኒ።

ማረኝ ይቅር በለኝ አለ ንዑ ኀቤየ ቡሩካኑ ለአቡየ የሚያሰኝኝ ይሁን እንጂ። አንድም ንዑ ኀቤየ ቡሩካኑ ለአቡየ ለመባል አድርግልኝ እንጂ።

ወሀበኒ ቦቱ ሥርየተ ኃጢአትየ።

በሥጋህ በደምህ ኃጢአቴን አስተሥርይልኝ።

ወሕይወተ ነፍስየ።

ሕይወተ ነፍስንም ስጠኝ፤

ኦ ሕይወተ ዓለም።

አቤቱ የድኅነት መገኛ።

በስእለታ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል በክልኤ ማርያም ወላዲትከ።

በወለደችህ ንዕድ ክብርት በሰማይ በምድር ብፅዕት በነፍስ በሥጋ ድንግል በምትሆን በእመቤታችን አማላጅነት፤

ወዮሐንስ መጥምቅ።

በመጥምቁ በዮሐንስ አማላጅነት።

ወበጸሎተ ኵሎሙ ቅዱሳን መላእክት።

ንዑዳን ክቡራን በሚሆኑ በመላእክት አማላጅነት፤

ወኵሎሙ ሰማዕታት ወጻድቃን መስተጋድላን ለሠናይ።

ለበጎ ነገር በሚጋደሉ በጻድቃን በሰማዕታት አማላጅነት ሕይወተ ነፍስን ስጠኝ። ለክፉ ነገር ተጋድሎ አለና ከዚያ ሲለይ መስተጋድላን ለሠናይ አሰ።

እስከ ለዓለመ ዓለም አሜን።

እንዳለፈው ነው።

Scanned by CamScanner

ወእንዘ ይትሜጦ ይኩ. ለባሕቲቱ።

ቄሱ ይህን ሲቀበል የብቻው ጸሎት ነው።

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ።

አቤቱ ፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ።

ኢይኩን ዝንቱ ምሥጢርከ አበሳ ላዕሌየ።

የተቀበልሁት ሥጋው ደመ ሳትበቃ ተቀበልህ ብሎ ዕዳ በደል አይሁንብኝ።

አላ ይኩን ለአንጽሖ ነፍስየ ወሥጋየ።

በነፍስ በሥጋ የሚያነጻኝ ይሁን እንጂ ይበል።

ወእምዝ ይትመጦ ቅድመ ቍርባን ለሊሁ።

ከዚህ በኋላ ሠራዒው ቄስ ራሱ አስቀድሞ ይቀበለው ጌታ ተቀብሎ የማቀበሉ ምሳሌ ነውና።

ወካዕበ ይመጡ ለንፍቅ ካህን።

ዳግመኛ ለተራዳዒው ቄስ ሥጋውን ያቀብል።

ወንፍቅሂ የሀቦ ደመ ለካህን።

ንፍቁ ቄስ ለሠራዒው ቄስ ደሙን ያቀብለው የተቀዳደመ ንባብ ነው የሚቀበለውስ ሠራዒው ቄስ ሥጋውን በገዛ እጁ ተቀብሎ ንፍቁ ቄስ ደሙን ያቀብለዋል ከዚህ በኋላ ሠራዒው ለተራዳኢው ቄስ ሥጋውን ያቀብለዋል ከዚህ በኋላ ንፍቁ ቄስ ደሙን በገዛ እጁ ይቀበላል።

ወእምዝ ይንሣዕ ለሊሁ በእዴሁ ደመ ንፍቅ ካህን።

ከዚህ በኋላ ተራዳኢው ቄስ ደሙን በገዛ እጁ ይቀበል።

ወእምዝ ይመጡ ለካህናት ውእቱ ካህን ሥጋ ወንፍቅሂ ደመ።

ከዚህ በኋላ ሠራዒው ቄስ ሥጋውን፣ ንፍቁ ቄስ ደሙን ለካህናት ያቀብሉ። ወቀሳውስትስ ይትመጠዉ እመስቀል ማዕከላይ ይላል። ቀሳውስት የመሐከለኛውን መስቀል ይቀበሉ ቆራቢ ያነሰ እንደሆነ መስቀል መስቀሉን አንሥቶ ያቀብላቸዋል መከራ እንቀበላለን ሲሉ ነው፤ ቆራቢ የበዛ እንደሆነ ከመስቀሉ እየጨመረ ክበቡን ያቀብላቸዋል።

Scanned by CamScanner

ይ.ካ. አንዘ ይሜጡ።

ካህኑ ሲያቀብል።

በቅዳሴ እግዚእነ ሥጋሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቀድሶ ነፍስ ወሥጋ ወመንፈስ።

በቅዳሴ እግዚእ ሥጋሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቀድሶ ነፍስ ወሥጋ ወመንፈስ ብሎ ያቀብል ጎድረት ነው እንጂ ሥጋ አምላክ አልሆነም ዕሩቅ ብእሲ ነው የሚሉ መናፍቃን አሉና ሥጋሁ ለእግዚእነ አለ የዕሩቅ ብእሲ ሥጋ ቢበሉት ይተኩሳል ደዌ ይሆናል የዕሩቅ ብእሲ ደም ቢጠጡት ይመራል እንጂ ሕይወትን ይሆናል? ለማለት ነው።

ወበቅዳሴ ሐዋርያት ጎብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት ቅዱስ ሥጋሁ ለክርስቶስ።

በቅዳሴ ሐዋርያት ጎበስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት ቅዱስ ሥጋሁ ለክርስቶስ ብሎ ያቀብል መለኮት ሰው አልሆነም ይላሉና ወረደ እምሰማይ አለ ጎበስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት እንዳለው ነው።

ወበቅዳሴ ሊቃውንት ሥጋሁ ለአማኑኤል አምላክነ ዘበአማን ዘነሥአ እምእግዝእተ ኩልነ ማርያም።

በቅዳሴ ሊቃውንት ከማርያም የነሣው የፈጣሪያችን የአማኑኤል ሥጋ ይህ ነው ብሎ ያቀብል። አማኑኤል ማለት አምላክ ወሰብእ ማለት ነው። ወዝ ስም ዐቢይ ጥቀ ዘኢይክሉ ፈሊጠቶ ወውእቱ ዘበአማን ምሥጢር ለጸንዐ ሃይማኖት። አንድም አማኑኤል ማለት አምላክ እግዚአብሔር ምስሌነ ማለት ነው። ሥጋ በቅድምና ነበር ባሕርዩን አግዘፎ ታየ ከሰማይ ሥጋ ይዞ ወረደ ከማርያም ሥጋ አልነሣም የሚሉ መናፍቃን አሉና ዘነሥአ እምእግዝእተ ኩልነ ማርያም አለ።

ዘይቁርብሂ ይበል አሜን።

የሚቀበልም ሥጋሁ ለእግዚእነ ብሎ ነበርና የጌታ ሥጋ መሆኑ። ጎበስተ ሕይወት ዘወረደ ብሎ ነበርና ጎበስተ ሕይወት መሆኑ። ሥጋሁ ለአማኑኤል ብሎ ነበርና የአማኑኤል ሥጋ መሆኑ እውነት ነው ይበል። ከዚህ በኋላ አቡነ ዘበሰማያት፣ ኑዛዜ፣ ሰላም ለኪ ብለህ መልክዐ ቍርባን አግባ።

ቅድመ ይቅረቡ ሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳት ወኤጲስ ቆጶሳት።

አስቀድመው ሠራዕያን እንደ መሆናቸው ሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳት ይቀበሉ።

Scanned by CamScanner

ወእምድኅሬሁሙ ቀሳውስት ወዲያቆናት፡፡

ከነሱ ቀጥለው ከነሱ በኋላ ቀሳውስት ዲያቆናት ይቀበሉ፡፡

ወካዕበ ኵሎሙ በበመዐርጊሆሙ፡፡

ዳግመኛም ሁሉም በየማዕርጋቸው ይቀበሉ፡፡

ወእምድኅረ እደው ይትመጠዋ አንስት፡፡

ከወንዶች ቀጥለው ከወንዶች በኋላ ሴቶች ይቀበሉ፡፡

ሕፃናትሰ እለ ይጠመቁ ይትመጠዉ እምቅድመ ሕዝብ፡፡

በአርባ ቀን በሰማንያ ቀን የሚጠመቁ ሕፃናት ግን ከሁሉ አስቀድመው ይቀበሉ፡፡ የዕለት ሹማምንት ናቸውና፡፡ አንድም በንጽሐ ጠባይዕ ያሉ ናቸውና፡፡ አንድም በንጽሐ ጠባይዕ መላእክትን ይመስላሉና፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ የአርባ ቀን ሕፃናት ይቀበላሉ፤ ከነዚህ ቀጥሎ የስድስት የሰባት ዓመት ሕፃናት ትንሾቹ እንደ ዕድሜያቸው ይቀበላሉ፤ ከነዚያ ቀጥሎ በድንግልና ኖረው የመነኰሱ ደናግል ይቀበላሉ፤ ከነዚያ ቀጥለው ኻያ፤ ኻያ ሁለት ዓመት የሆናቸው ደናግል ይቀበላሉ፡፡ ከነዚያ ቀጥሎ በሹመት ያሉ ናቸውና ንፍቀ ዲያቆናት አናጉንስጢሳውያን መዘምራን፣ ዐፀውተ ኃዋኅው ይቀበላሉ፤ ከነዚያ ቀጥሎ በሕግ ኖረው የመነኰሱ መነኮሳት ይቀበላሉ፤ ከነዚያ ቀጥሎ በንስሐ ተመልሰው የመነኮሱ መነኰሳት ይቀበላሉ፡፡ ከነዚያ ቀጥሎ በሕግ ጸንተው ያሉ ሕጋውያን በየማዕርጋቸው ይቀበላሉ ሴቶችም ከሁሉ አስቀድሞ የሰማንያ ቀን ሕፃናት ይቀበላሉ፤ በንጽሐ ጠባይዕ ያሉ ናቸውና፡፡ አንድም በንጽሐ ጠባይዕ መላእክትን ይመስላሉና፡፡ አንድም የዕለቱ ሹማምንት ናቸውና፡፡ ከነዚያ ቀጥለው የስድስት የሰባት ዓመት ሕፃናት እንደ ዕድሜያቸው ሕፃናቱ አስቀድመው ታላላቆቹ ቀጥለው ይቀበላሉ፡፡ ከነዚያ ቀጥለው በድንግልና ኖረው የመነኮሱ ደናግል በመሐከል ይቆማሉ በፊት ይቀበላሉ፡፡ ከነዚያ ቀጥለው ዐሥራ ሁለት ዐሥራ አምስት ዓመት የሆናቸው ደናግል ይቀበላሉ፡፡ ከነዚያ ቀጥለው የቀሳውስት ሚስቶች ይቀበላሉ ከነዚያ ቀጥለው በሕግ ኑረው የመነኰሱ ይቀበላሉ፡፡ ከነዚያ ቀጥለው የዲያቆናት ሚስቶች ይቀበላሉ፡፡ ከነዚያ ቀጥለው በንስሐ ተመልሰው የመነኰሱ መነኮሳት ይቀበላሉ ከነዚያ ቀጥለው የንፍቀ ዲያቆናት የአናጉንስጢሳውያን የመዘምራን ሚስቶች ይቀበላሉ ከነዚያ ቀጥለው በሕግ ጸንተው ያሉ ሕጋውያን

ይቀበላሉ፡፡ ከነዚያ ቀጥለው የንስሐ ሕዝባውያን ሚስቶች በየማፅረጋቸው ይቀበላሉ፡፡ ወለእመ ሖረ ካህን ኀበ ድውይ ከመ ያቍርብ ቁርባነ ኢይመጥዎ ለሕያው ይላል ሰው ታሞ ሊያቀብል በሄደ ጊዜ የታመመው ወንድ ቢሆን ሴቲቱ አንድ አካል አይደለንም ለምን እለያለሁ እኔም ከዚህ እቀበላለሁ አትበል የታመመችው ሴት ብትሆን ወንድየው ብእሲ ወብእሲት አሐዱ አካል እሙንቱ ይላል አንድ አካል አይደለንም? መች እንለያያለን እኔም ከዚህ ልቀበል አይበል፡፡ ድውይ ከዚያ ይቀበል ሕያው የሆነ ከቤተ ክርስቲያን መጥቶ ይቀበል፡፡ ሌላውም ከመንገድ እኔ ከዚህ ካገኘሁ መንገዱን ትርፌ እኔም ከዚሁ ልቀበል አይበል ከቤተ ክርስቲያን ሄዶ ይቀበል፡፡ ወይኩን ተመጣዌ ቍርባን ዕሩቀ ርእስ ወምስቍለ እድ ይላል፡፡ የሚቀበለውም ሰው ንጉሥ ቢሆን ዘውዱን ካህን ቢሆን መጠምጠሚያውን ህባኔውን ቀጸላውን ያውርድ ሴት ብትሆን ሰርመዲዋን ክንብንቧን አውርዳ ይቀበሉ ቀዳሹ ቄስ ቢሆን ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስ፣ ኤጲስ ቆጶስ፣ ቆሞስም ቢሆን ሥጋውን በዕርፈ መስቀል አኑሮለት በዕርፈ መስቀል አንሥቶ ይቀበል፡፡

ወእምድኅረ ተመጥዎ ቍርባን እንዘ ሀሎ በአፉሁ ይበል ኵሉ ለለ አሐዱ አሐዱ፡፡

ሥጋውን ተቀብሎ ባፉ ሳለ ይህን ጸሎተ ኅሊና ደግሞ ይላከው ሁሉም ለእያንዳንዱ ይህን ይድገም ከሰባቱ ኪዳናት አንዱ ይህ ነው የስድስቱን ምክንያቱን በየደጁ ይናገራል ይህን ሥጋውን ተቀብሎ ባፉ ይዞ ጸሎተ ኅሊና ደግሞ ሊላኩት ከፍለውናል፡፡ የከፈሉት ሐዋርያት ናቸው አንድም የኋላ ሊቃውንት ናቸው፡፡ አንድም ባስልዮስ ነው፡፡

ይበል ዲያቆን እንዘ ይትሜጦ ጽዋዐ፡፡

ዲያቆን ጽዋውን ከንፍቁ ቄስ ሲቀበል፡፡

ጽዋዐ ሕይወት እትሜጦ፡፡

ሕይወት የሚያድለውን ጽዋ እቀበላለሁ፡፡

ወስመ እግዚአብሔር እጼውዕ፡፡

የእግዚአብሔርን ስም ጠርቼ አመሰግናለሁ ብሎ ይቀበል፡፡

ወእምዝ ይበል፡፡

ከዚህ በኋላ እንዲህ ይበል፡፡

ጸልዩ በእንቲአነ ወበእንተ ዘኵሎሙ ክርስቲያን አለ ይቤሉነ ግበሩ ተዝካሮሙ::

ስለኛ የታመሙትን ፈውስ የሞቱትን አስነሣ ብላችሁ አትርሷቸው ስላሉን ምእመናን ሁሉ ጸልዩ ይበል::

በሰላም::

በአንድነት በመስማማት::

ወበፍቅረ አየሱስ ክርስቶስ::

ኢየሱስ ክርስቶስ አንተሙሰ ሶበ ትጼልዩ ከመዝ በሉ:: አቡነ ዘበሰማያት ብሎ ባደረገው ባዘዘው ፍቅር:: ኢታብአነ ውስተ መንሱት ብሎ አንዱ ለብዙ አንዱ ላንዱ መጸለይ ፍቅር ነው እንጂ፤ ፍቅር ነውና እንዲህ አለ::

ሰቦአ::

አመሰግኑ::

ወዘምሩ::

ዳዊት ድገሙ አንድም ሰብሑ ወዘምሩ:: እያመሰገናችሁ ዳዊት ድገሙ:: አንድም ዳዊት እየደገማችሁ አመስግኑ ይበል::

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሥሉስ ዘኢይትነገር::

የማይመረመር ልዩ ሦስት:: የማይመረመር አለ በአካል በስም ሦስት ሲሆኑ በባሕርይ በመለኮት አንድ መሆናቸው አይመረመርምና:: ልዩ ሦስት አለ፤ አንድም ባንድነቱ ምንታዌ በሦስትነቱ ርባዔ የለበትምና:: አንድም ለፀሓይ ለቀላይ ለእሳት የግበር ሦስትነት ቢኖራቸው የባሕርይ የህልውና አንድነት የአካል ሦስትነት የላቸውም ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ለጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ለስልዋኖስ የአካል የስም ሦስትነት ቢኖራቸው የህልውና አንድነት የላቸውም፤ ሥላሴ ግን በአካል በስም ሦስት በባሕርይ በህልውና አንድ ናቸውና:: አንድም ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ለጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ለስልዋኖስ መከታተል አለባቸው፤ ሥላሴ ግን በአንድነታቸው መከታተል የለባቸውምና:: ኢሀሎ አብ አሐተ ሰዓተ ወኢ ከመ ቅጽበተ ዓይን ዘእንበለ ወልደ ወመንፈስ ቅዱስ ወኢሀሎ ወልድ አሐተ ሰዓተ ወኢ ከመ ቅጽበተ ዓይን ዘእንበለ አብ ወመንፈስ ወኢሀሎ መንፈስ ቅዱስ አሐተ ሰዓተ ወኢ ከመ ቅጽበተ ዓይን ዘእንበለ አብ ወወልድ አላ ሥሉስ ቅዱስ

ፅሩያን ህልዋን ወትረ ዘእንበለ ጥንት ወኢተፍጻሜት[132] እንዲል። አንድም ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ለጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ለስልዋኖስ መቀዳደም አለባቸው፤ ሥላሴ ግን በአንድነታቸው መቀዳደም የለባቸውምና፤ አሐቲ ይእቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ ዕሩያን እሙንቱ በቅድምና[133] እንዲል።

ሀበኒ ክመ እንሣእ ለሕይወት ዘንተ ሥጋ ወደመ ዘእንበለ ኵነኔ።

ሳይፈረድብኝ ይህን ሥጋውን ደሙን ሕይወተ ሥጋ ሕይወተ ነፍስ ሊሆነኝ እቀበል ዘንድ መቀበሉን ስጠኝ ሥጋውንስ ተቀብሏል ደሙን ሲያይ ነው። አንድም የተቀበልሁት ሥጋውን ደሙን አዋሕድልኝ ሲል ነው አንድም ያለ ኵነኔ ነፍስ እኖር ዘንድ ሥጋውን ደሙን መቀበሉን ፍቀድልኝ ነው።

ሀበኒ እግበር ፍሬ ዘያሠምረክ።

ደስ የሚያሰኝህን ፍሬ ሃይማኖት አፈራ ዘንድ ምግባረ ነፍስ እሠራ ዘንድ መሥራቱን ስጠን ከመ አስተርኢ በስብሐቲክ። በጎ ሥራ ሠርቼ በክብርህ ከብሬ እታይ ዘንድ አንድም አመሰግንህ ዘንድ።

ወእሕየው ለክ እንዘ እገብር ዘዚአክ ፈቃደ።

ሕያው ሁኜ ላንተ ምግባረ ነፍስ እየሠራሁ ምሥጋና ሳቀርብ እኖር ዘንድ። አንድም አንተን አመሰግኜ እድን ዘንድ።

በተአምኖ እጼውዐከ አበ።

አምላክነትህን በማመን አንድም የባሕርይ አባትነትህን አምኜ አቡነ ዘበሰማያት ብዬ እለምንሃለሁ እጠራሃለሁ።

ወእጼውዕ መንሥትከ።

ጌትነትህንም እለምናለሁ አብ! ሰማያዊ አባቴ አንተን እለምንሃለሁ። መንፈስ ቅዱስ ይምጣልኝ ብዬ አንድም ትምጻእ መንግሥትከ ብዬ እለምንሃለሁ።

---

[132] አብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ የዓይን ጥቅሻ ጊዜ ያህል እንኳ አልኖረም፤ ወልድም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ የዓይን ጥቅሻ ያህል ጊዜ እንኳን አልኖረም፤ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ተለይቶ የዓይን ጥቅሻ ያህል ጊዜ እንኳ አልኖረም፤ ሥሉስ ቅዱስ ጥንት ፍጻሜ ሳይኖራቸውም ዘለዓለም በአንድነት ጸንተው ይኖራሉ እንጂ። ሃይማኖተ አበው ዘሳዊሮስ ገጽ ፥ ፯

[133] መጽሐፈ አክሲማሮስ

ይትቀደስ እግዚኦ ስምከ በላዕሌነ፡፡

አቤቱ ስመ አምላክነትህን ግለጥልን፡፡ ስመ አምላክነቱን ካላወቁ እሉ ሕዝብ በአፉሆሙ ያከብሩኒ ወበልቦሙሰ ነዋኃ ይርሕቁ እንደተባሉት እንደ እስራኤል መሆን ነውና፡፡[134] አንድም ስመ ወላዲነትህን ግለጥልን፡፡ ስመ ወላዲነቱን ካላወቁ አቡክሙ አነ ወአንትሙ ክህድክሙኒ እንዳላቸው እንደ እስራኤል መሆነ ነውና፡፡[135] አንድም ስመ ወላዲነትህን ስመ ተወላዲነትህን ስመ ሠራዒነትህን ግለጥልን፡፡

እስመ ኀያል አንተ እኵት ወስቡሕ፡፡

ይህን ዓለም እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ አምጥተህ የፈጠርህ፡፡ አንድም እምኀበ ቦ ኀበ አልቦ የምታሳልፍ ኀያል ከሃሊ አንተ ነህና እኵት ስቡሕ ተብለህ የምትመሰገን አንተ ነህና፡፡ አንድም የምትመሰገን ኀያል አንተ ነህና አቤቱ ስመ አምላክነትህን ግለጥልን፡፡

ወለከ ስብሐት ለዓለመ ዓለም፡፡

ላንተ ክብር ምስጋና ይገባሃል፡፡

ወእምዝ ይብላዕ ዘተመጠወ፡፡

ይህን ከጸለየ በኋላ የተቀበለውን ይላከው፡፡

ወጊዜ ተመጥዎቱ፡፡

በተቀበለ ጊዜ፡፡

ይደሉ ከመ ያንብር እዴሁ ዲበ አፉሁ ወይሂኮ በለሆሳስ፡፡ እስከ ያጸሪ አፉሁ በፍርሃት ወበረዐድ፡፡

ያንብር እዴሁ ዲበ አፉሁ እስከ ያጸሪ አፉሁ ወይሒክ በለሆሳስ በፍርሃት ወበረዐድ ብለህ ይግጠም፡፡ እጁን ካፉ ላይ ማኖር ይገባዋል ለመጠንቀቅ ነው እጁን ካፉ ላይ አኑሮ በፍርሃት በረዓድ ሁኖ እንዳይነጥብ እስኪያጸራ ቀስ ቀስ ብሎ ይላከው ከጥርስና ከጥርስ መካከል ከትናጋ ተላኮ እንዳይቀር ነው፡፡ እመቤታችን ለአንድ ዲያቆን እንደነገረችው ደፍሮ ሳይፈራ ሲያላምጠው አይታ አንተ ደፋር ዲያቆን የልጄ ሥጋ ነው እንጂ እንደ ሌላ ምግብ ታደርገዋለህን ብላዋለች

---

134 ይህ ሕዝብ በከንፈሮቹ ያከብረኛል፣ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነውና፣ በከንቱ ያመልኩኛልና፣ ሰው ሠራሽ ትምህርት ያስተምራሉ፡፡ ኢሳይያስ ፳፱ ፡ ፲፫

135 ትንቢተ ኢሳይያስ ፩ ፡ ፪

ያመፈትሁትውን ካህን ትላልቅ አርጎ አይፈትት እጅግም ሳያበዛ እጅግም ሲያሳንስ በመጠን በመጠን አድርጎ ይፈትት። የበዛ እንደ ሆነ አዙሮ ለመላክ ያውክል አይመችም መሰና መቃብር አለበት ያስኛልና። ያነሰ እንደሆነ ለጊዜው ከትናጋ ተላክ ይቀራል። ፍጻሜው ግን ሕፀፅ አለበት ያስኛልና በፍርድ መጽሐፍ አማርኛ መለኮት አልተዋሐደም ይላል ወኢይፍትት ዐቢያተ ከመ ኢይትፈዐምዎ ክልኤተ ጊዜ ዳዕመ ይኩን ዐቅመ ዘየዐውድ ወውሳጤ ከናፍር ወከናፍረሁኒ ለዘይትሜጠ ይኩና ጥቡቃተ በፍርሃት ወበረዓድ ከመ ኢይደቅ እምኔሁ ምንትኒ ወከመ ኢያምስጎ እማዕከለ አስናኒሁ እንዲል።

ወእምዝ በልዎ ምላእ አፉየ ስብሐቲከ ወልብየ ኃሜተ ወነፍስየ ትፍሥሕተ።

ሥጋውን ተቀብለሙ ወደ ደሙ ስሔድ ፈጽሞ ደስ ብሎኝ በነፍስ በሥጋ እንዳመሰግንህ አድርገኝ።

ለዘተመጠዉኩ እምዝንቱ ምስጢር።

አምላካዊ መለኮት የተዋሐደው ሥጋውን ደሙን ከመቀበሌ የተነሣ። አንድም ሥጋውን ደሙን የተቀበልሁ እኔ የጌትነትህን ምሥጋና እንዳመሰግን አድርገኝ፤ አንድም የነፍስ የሥጋ ተድላ ደስታን አሳድርብኝ ይበል።

ዘኮነ ሰብአ በእንተ መድኃኒተ ሰብእ።

ሰውን ለማዳን ሰው የሆነ መለኮት የተዋሐደው ሥጋው ደሙን የተቀበልሁ አንድም ከመቀበሌ የተነሣ።

ወይበል ንፍቅ ቀሲስ እንዘ ይሜጡ ደመ።

ንፍቅ ቄስ ደሙን ሲያቀብል።

ዝንቱ ጽዋዐ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት ክቡር ደመ ለክርስቶስ።

ከሰማይ የወረደ ሕይወትን የሚያድል የክርስቶስ ደሙ ይህ ነው። አንድም ከሰማይ የወረደ የክርስቶስ ደሙ ይህ ጽዋዕ ነው። አንድም የክርስቶስ ደም የሚሆን ይህ ጽዋዕ ከሰማይ የወረደ ነው ብሎ ያቀብል።

ወዘይትሜጠ።

የሚቀበለውም።

ይበል አሜን ወአሜን።

እውነት ነው ከሰማይ የወረደ የክርስቶስ ደመ ነው ይበል። ሥጋውን ሲቀበል አንድ ጊዜ ደሙን ሲቀበል አሜን ወአሜን ማለቱ ሦስት መሆኑ የሥስትነት ቃሉ አለመለወጡ የአንድነት ምሳሌ። አንድም ከዚያ አንድ ጊዜ አሜን ማለቱ ሥጋውን እንደተቀበለ ከዚህ ሁለት ጊዜ አሜን ወአሜን ማለቱ ሥጋውንም ደሙንም እንደተቀበለ ለማጠየቅ። አንድም በሦስት ወገን በሥጋ፣ በደማዊት ነፍስ፣ በነባቢት ነፍስ እንደ ካሰልን ለማጠየቅ። አንድም በደም ሁለት ጊዜ መሆኑ ነባቢት ነፍስ አትበላም፤ በነባቢት ነፍስ የካሰልንን በሥጋ በደማዊት ነፍስ እንቀበለዋለንና። አንድም ሁለት ጊዜ ከጎኑ ደም ፈሷልና ከሞት አስቀድሞ ከመላ ሕዋሳቱ ከሞት በኋላ ከጎኑ። አንድም ሐራዊ አለን የለም? ብሎ ጎኑን በወጋው ጊዜ ትኩስ ደም እንደ ሰ ፈደል ሆኖ በመካከል ውኃው ወርዷልና ጸሎት ዘባስልዮስ ወትእዛዝ ዘሀገርነ። ባስልዮስ የተናገረው ትእዛዝ ይህ ነው ትእዛዙ ግን የጌታችን ትእዛዝ ነው። ሥጋውን ተቀብሎ ባፉ ይዞ ቅዱስ ሥሉስን በጎሊና ደግሞ ሥጋውን እንዲላከው ደሙንም ተቀብሎ ባፉ ይዞ ይህ ጸሎተ ጎሊና ጸልዮ ይላከው ብለው ያዘዙ የሀገራችን መምህራን ናቸውና፤ ነገር ግን ደም በአፉ ይዞ መቆየት አይቻልምና ከተቀበለ በኋላ ይጸልይ። ወእንዘ ሀሎ ደም በአፉሁ ይበል በጎሊናሁ። ደሙን ተቀብሎ በአፉ ሳለ በጎሊናው እንዲህ ይበል ደም በአፉ ይዞ መጸለይ አይቻልምና በጎሊናሁ አለ ተቀብሎ ነው።

አ እግዚእየ ወአምላኪየ ኢየሱስ ክርስቶስ።

አቤቱ ፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ!

ናሁ ተመጠውኩ ሥጋከ ንጹሐ ወደመከ ክቡረ ይኩንኒ ለሥርየተ ኃጢአትየ ወበእንተ ኩሉ አበሳየ።

በነፍስ በሥጋ ስሠራሁት ለኃጢአት ማስተሥረይ ይሆነኝ ዘንድ ንጹሕ ክቡር የሚሆን ሥጋህን ደምህን እነሆ ተቀበልሁ፤ አንድም የተቀበልሁት ንጹሕ ክቡር የሚሆን ሥጋህ ደምህ በነፍስ በሥጋ በሠራሁት ኃጢአት ማስተሥረይ ይሁነኝ።

Scanned by CamScanner

ወልድ ዋሕድ ወመፍቀሬ ሰብእ፡፡

ተቀዳሚ ተከታይ የሌለህ ሰው ወዳጅ የምትሆን ወልድ፡፡

ምላእ አፉየ ስብሐቲከ ከመ እሰብሕ አኰቴተከ፡፡

ምስጋናህን እናገር ዘንድ እንዳመሰግንህ አድርገኝ አንድም ጌትነትህን እናገር ዘንድ እንድናገር አድርገኝ፡፡

እስመ አንተ ቀዳሚ ዘተሰባእከ ወተሰባሕከ ቦቱ፡፡

አምስት ሽሕ ከአምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ሰው የሆንህ አንተ ነህና በሥጋ የተመሰገንህ ሰባሕኩከ ወዓዲ ካዕበ እሴብሐከ ተብለህ፡፡ አንድም በሥጋ የተገለጥህ፡፡ አንድም በሥጋ የተሰቀልህ አንተ ነህና እስመ ዓዲሁ ኢወረደ መንፈስ ቅዱስ በእንተ ዘኢተሰብሐ እግዚእ ኢየሱስ እንዲል፡፡[136]

ከመ ታድኅነኒ እስከ ለዓለም፡፡

እስከ ዘለዓለሙ ታድነኝ ዘንድ፡፡

ወአድኅንከኒ በእንተ ስምከ ቅዱስ ለዓለመ ዓለም ታድኅነኒ ብሎ ነበር ክቡር ጽኑ በሚሆን ስምህ ስላመንሁ፡፡ አንድም ስለ ተጠራሁ፡፡ አንድም ስምህን ስላስተማርሁ ለዘለዓለሙ አዳንኸኝ፡፡

ስብሐት ለከ ኦ እግዚእየ ወአምላኪየ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡

አቤቱ ፈጣሪዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ላንተ ክብር ምስጋና ይገባሃል፡፡

ዘወሀብከኒ ዕሩየ በእደ ዚአሁ ለገብርከ እገሌ፡፡

የቄሱን ስም ጠርቶ ባገልጋይህ በዕገሌ እጅ ሥጋውን ከደሙ ደሙን ከሥጋው አንድ አድርገህ፤ አንድም ከምሴተ ኀሙስ ከዕለተ ዐርብ ጋር አንድ አድርገህ የሰጠኸኝ፡፡

እሴብሐከ ወእስእለከ ከመ እኩን ውስተ መርዔትከ ወከመ ትኑልቈኒ ምስለ አባግዒከ፡፡

መርዔትከና አባግዒከአንድ ወገን ከምእመናን ጋራ አንድ ታደርገኝ ዘንድ ፈጽሜ እለምንሃለሁ፡፡ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ከመ ያዕትት እዴሁ እምላዕሌክሙ እንዲል፡፡

---

[136] ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ቅዱስ ገና አልወረደም ነበር፡፡ ዮሐንስ ፯ ፡ ፴፱ (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ገና ስላልተሰቀለ መንፈስ ቅዱስ አልተሰጠም ነበር፡፡ አንድምታ)

ወተወክፈኒ፡፡

በጸጋ በረድኤት በይቅርታ በቸርነት ተቀበለኝ፡፡

ይእዜኒ ኢትዝክር ሊተ አበሳየ፡፡

የቀደመው ኃጢአቴን አትዘክርብኝ ይቅር በለኝ፡፡

አአኵቶ ለጸጋ ዚአከ ዘተውህበ ሊተ ወለረድኤትከ እንተ ኮነት ምስሌየ፡፡

የሰጠኸኝ ጸጋህን በኔ አድራ ያለች ረድኤትህንም አመሰግናለሁ፡፡ አንድም ጸጋውን ስለሰጠኸኝ በእኔ አድራ ያለች ረድኤትህንም ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ (ምስሌየ) ሊተ ሲል ነው፡፡

ወእምዝ ይዘምሩ ካህናት በስብሐት መዝሙር፡፡

ከዚህ በኋላ ካህናት መዝሙር በሚባል ምስጋና ያመስግኑ፡፡ ዳዊት ይድገሙ ማለት ነው፡፡

ወኢያጽርዑ፡፡

አያስታጉሉ፡፡

አላ በበአሐዱ፡፡

አንድ አንድ ሆነው፡፡

አው በበክልኤቱ ይዘምሩ፡፡

ወይም ሁለት ሁለት ሆነው ይድገሙ እንጂ፡፡

ትእዛዝ፡፡

ከዚህ መቶ ሃምሳ ዳዊት ታዟልና ተከፋፍሎ መድገም ይገባል፡፡ የማይችል ቢሆን ግን ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር በቅዱሳኑ መድገም ይገባል፡፡ ይህ ግን ሰው ቢታጣ ነው፡፡

ይ.ካ.. እንዘ ይወፅእ እለ ጸዋዕከ እግዚኦ፡፡

ቄሱ ሲወጣ ንዑ ትልዉኒ ብለህ በሃይማኖት የጠራሃቸውን፡፡

ወእለ ቀደሰከ፡፡

ከክህደት የለየኻቸውን፤

ክፍል በሎጥዓከ።

ንዑ ትልዉኒ ብለህ ከክህደት ወደ ሃይማኖት በመጥራትህ አክብራቸው። አንድም እለ ጸዋዕከ አግዚኦ፤ ወደ ሃይማኖት የጠራኻቸውን።ወእለ ቀደስከ። በልጅነት ያከበርኻቸውን ለይ።

በጽዋዓከ።

ንዑ ብልዑ ኀብስትየ ወስትዩ ወይንየ ብለህ በመጥራትህ ለሥጋው ለደሙ አብቃቸው።

ወአጽንዕ ቦኑይልከ።

በአሃሊነትህ ጠብቃቸው።

ወዕቀብ በፍቅርከ።

በፍቅርህ አጽናቸው።

ወይምር ውስተ ዘለዓለም መንግሥትከ በክርስቶስ።

በክርስቶስ አዳይነት ሰጭነት በመንግሥተ ሰማይ አንድ አድርጋቸው ይበል።

ዘቦቱ ለከ በል ወይዕቅብ እንዘ ይወዕእ ዲበ ዛሕል አሐዱ ጊዜ።

ሲወጣ በዓሕሉ ላይ አንድ ጊዜ ይባርክ። ቡራኬው የአፍአ ነው ነገር ግን እጁ ከውስጥ ከገባ በኋላ አይወጣምና ነው እንጂ እጁ በውስጥ እንዳለ ነው። ይህን ሦስት ጊዜ ያሉ እንደሆነ ረዓዮሙን አንድ ጊዜ ይሏል።

ወአምዝ መጡ ውእቱ ካህን ሥጋ።

ከዚህ በኋላ ሠራዒው ቄስ ሥጋውን።

ወዲያቆን ደመ።

ዲያቆን ደሙን ለሕዝቡ ያቀብል። ወኢይመጡ ዲያቆን ለካህን ይላል በዕርግና በደዌ ምክንያት ከቅድስት የተቀመጠ ካህን ቢኖር ተራዳኢው ቄስ ያቀብለው እንጂ ዲያቆን ደሙን አያቀብለው ዲያቆንም ቄስ አቀብል ብሎ ቢያዘው ነው እንጂ ማቀበል አይገባም በዕርፈ መስቀል እንጂ በእጁም ማቀበል አይገባም። ዲያቆን ኢይባርክ ወኢያቅርብ በእዴሁ ዘእንበለ እምጽዋዕ በዕርፈ መስቀል እንዲል።

Scanned by CamScanner

ወእንዘ ይሜጡ ይበል ከመ ቀዳሚ፡፡

ሲያቀብል እንደ ቀደመው በቅዳሴ እግዚእ ሥጋሁ ለእግዚእነ በቅዳሴ ሐዋርያት ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት፡፡ በቅዳሴ ሊቃውንት ሥጋሁ ለአማኑኤል አምላክነ ብሎ ያቀብል፡፡

ወሕዝብኒ እንዘ ይትሜጠው፡፡

ሕዝቡም ሲቀበሉ፡፡

ይበሉ አሜን አሐደ ጊዜ ዲበ ሥጋ፡፡

በሥጋው አንድ ጊዜ አሜን፡፡

ወክልኤተ ጊዜ ዲበ ደም፡፡

በደሙ ሁለት ጊዜ አሜን ወአሜን ይበሉ፡፡ ከሥጋው ጋራ ሦስት ይሆናል ለቀድሶ ነፍስ፣ ወሥጋ፣ ወመንፈስ ብሎ ያቀብላልና፡፡ የቀረው እንዳለፈው ነው፡፡ ከዚህ በደዌ በዕርግና ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን መምጣት የማይቻለው ሆኖ ሥጋውን ደሙን አቀብሉኝ ቢል ከቤተ ክርስቲያን ያሉ ምእመናን ከተቀበሉ በኋላ ሄደው ሊያቀብሉት ይገባል ከዚህ በኋላ ተመልሰው ጸሎታቸውን ይፈጽሙ፡፡

ወአምድኅረ ተመጠዉ ሕዝብ፡፡

ሕዝቡ ከተቀበሉ በኋላ ጸሎቱ የሕዝቡ ነውና ፊቱን ወደ ሕዝቡ እንደ መለሰ፡፡

ይ.ካ. እግዚአብሔር ዘለዓለም፡፡

አነጋገሩ ከአብ ጋራ ነው አቤቱ ኅልፈት ውላጤ የሌለብህ፡፡

ብርሃነ ሕይወት፡፡

የሕይወት መገለጫ የምትሆን

እግዚአብሔር ዘወሀብከነ እግዚኦ ለአግብርቲከ ጽንዐተ ወዕቅበተ በዘሀሎ ዕለታት ወለያልይ፡፡

አቤቱ ለኛ ለባሮችህ ላገልጋዮችህ ጽንዐትን መጠበቅን ሰጠኸን አለ በነበረው መዐልት በነበረው ሌሊት አጽንተህ ጠብቀኸናልና፡፡

እንዘ ተዐቅብ በሰላም፡፡

በፍቅር ባንድነት አጽንተህ ጠብቀኸናልና፡፡

Scanned by CamScanner

ባርክ በዘይእዜ መዋዕል ወበዘይመጽእ እምድኅር::

አሁንም ባለው ዕለት ባለው ሰዓት አክብረን ጠብቀን ከዚህ በኋላ በሚመጣውም ዘመን ጠብቀኸን ኑር::

በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ::

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነት ይበል ዘቦቱ ለከ በል::

ይ.ዲ. ነአኵቶ ለእግዚአብሔር ቅድሳቶ ነሢአነ ከመ ለሕይወተ ነፍስ ይኩነነ ፈውሰ::

ከዚህ በኋላ ዲያቆን ከዚህ ቀጥሎ ሕይወተ ነፍስ ሕይወተ ሥጋ ይሆነን ዘንድ ሥጋውን ደሙን የተቀበልን እኛ ሥጋውን ደሙን ተቀብለን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን:: አንድም ናዕኵቶ ይላል ሥጋውን ደሙን ተቀብለን እናመስግነው::

ዘተመጦነ ንስእል ወንትመሐፀን እንዘ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር አምላከነ::

ሥጋውን ደሙን የተቀበልን እኛ ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን እያመሰገነው እንለምናለን ሰማይ ሩቅ አደራ ጥብቅ እንዲሉ ነፍሳችንን አደራ እንላለን:: አንድም ዘተመጦነ እንዘ ንሴብሖ ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን እያመሰገን ሥጋውን ደሙን የተቀበልን እኛ እንለምናለን ነፍሳችንንም አደራ እንላለን:: አንድም እየለመንህ አደራ እያልን ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን እናመሰግነው ይበል::

ይ.ካ. ስብሐተ እግዚአብሔር ይነገር አፉየ::

ቄሱ አንደበቴ የእግዚአብሔርን ጌትነት ይናገራል ምስጋናውን ያመሰግናል ይበል የእግዚአብሔርን ጌትነቱን እናገራለሁ ሲል ነው::

ወኵሉ ዘሥጋ ይባርክ ለስሙ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም::

ሥጋዊ ደማዊ ፍጥረት ሁሉ ጽኑ ክቡር ልዩ ለሚሆን ስሙ ምስጋና ያቀርባል ያቅርብ ይበል::

ይ.ሕ. አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት::

ሕዝቡም አቤቱ ሰማያዊ አባታችን ወደ መከራ ወደ ገሃነም ወደ ኃጢአት ወደ ክህደት አታግባን ይበሉ::

Scanned by CamScanner

ይ.ዲ. ተመጦነ እምሥጋሁ ቅዱስ ወእምደሙ ክቡር ለክርስቶስ።

ተመጦነና ዘተመጦነ አንድ ወገን። የክርስቶስን ሥጋውን ደሙን። አንድም ከሥጋው ከደሙ የተቀበልን እኛ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን አንድም እናመሰግነው ይበል። ወዘ ውእቱ ደሞ ለክርስቶስ ይላል አብነት።

ይካ. ስብሐተ እግዚአብሔር ይነግር አፉየ ወኵሉ ዘሥጋ ይባርክ ለስሙ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም።

ትርጓሜው እንዳለፈው ነው።

ይ.ዲ. ወናእኵቶ ይደልወነ ከመ ንሳተፍ ምሥጢረ ክብርተ ወቅድስተ።

ሥጋውን ደሙን በመቀበል አንድ ሆነን ልናመሰግነው ይገባናል። አንድም ሥጋውን ደሙን እንዋሐድ ዘንድ ልናመሰግነው ይገባናል ይበል።

ይካ. ስብሐተ እግዚአብሔር ይነግር አፉየ።

ይ.ሕ. አቡነ ዘበሰማያት።

ትርጓሜው እንዳለፈው ነው።

ይካ. ለእመ ኮነ ፅዝል አሌፅለከ ንጥሥየ ወአምላኪየ።

ፅዝል ቢሆን አቤቱ ገቢዬ ፈጣሪዬ ልፅልናህን እናገራለሁ።

ወእባርክ ለስምከ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም።

ለዘለዓለመ ልዩ ጽኑዕ ክቡር ለሆነው ለገናናው ስም ሀምስጋና አቀርባለሁ ይበል።

ይ.ሕ. አቡነ ዘበሰማያት።

ትርጓሜው እንዳለፈው ነው።

ይካ. ኵሉ አሚረ እባርከከ።

ዘወትር አመሰግንሃለሁ። አንድም ክብርህን እናገራለሁ።

ወእሴብሕ ለስምከ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም።

በዚህ ዓለም በሚመጣውም ዓለም ለስምህ ምስጋና አቀርባለሁ ይበል።

ይ.ሕ. አቡነ ዘበሰማያት።

ትርጓሜው እንዳለፈው ነው።

Scanned by CamScanner

ይ.ካ. ስብሐተ እግዚአብሔር ይነግር አፋዩ።

ትርጓሜው እንዳለፈውነው።

ይ.ሕ. አቡነ ዘበሰማያት።

ትርጓሜው እንዳለፈው ነው፡

አኰ በሙሉ ዕዝል ዘይትበሃል።

ዕዝል በሚቀደስበት ጊዜ ሁሉ አሌዕለከ የሚባል አይደለም።

አላ በበዓላተ እግዚእነ ወበዓላተ እግዝእትነ ወበእሑድ ሰንበት።

በጌታ በዘጠኙ በዓላት፤ በእመቤታችን በዓላት፤ እሑድ እሑድ ዕዝልም ቢሆን በግዕዝም ቢሆን አሌዕለከ። በሌላው ቀን ዕዝልም ቢሆን ግዕዝም ቢሆን ስብሐተ እግዚአብሔር ይነግር አፋዩ ማለት ይገባል። ድርገት ሲወርድ መውደቅ እጅ መንሣት ይገባል። ስለምን ቢሉ ቅዱሳት አንስት ከመቃብር ደርሰው ሲመለሱ ወተራከቦን እግዚእ ኢየሱስ በፍኖት ወይቤሎን በሐክን ይላል። ጌታ ከመንገድ አግኝቷቸው እንዴት ሰነበታችሁ አላቸው። አኃዛ እገሪሁ ቀርባ ወሰገዳ ሎቱ ይላል። ከእግሩ ወድቀው ሰግደውለታልና የዚያ ምሳሌ። ድርገት ወደ ምዕራብ መውረዱ ጌታ ወደ እዚህ ዓለም የመምጣቱ ምሳሌ፤ ወደ ምሥራቅ መመለሱ የዕርገቱ ምሳሌ። አንድም ወደ ምዕራብ መውረዱ ጌታ ፊቱን ወደ ምዕራብ መልሶ ለመሰቀሉ ምሳሌ እስመ ገጹ ለእግዚአብሔር መንገለ ምዕራብ ከመ ይነጽር ኵሉ ሕዝብ መንገለ ብርሃኑ ዘይሠርቅ እንዲል። ወደ ምሥራቅ መመለሱ የትንሣኤ አምሳል ነው። ከወጡም በኋላ ዲያቆን አንድ ጊዜ ዞሮ ይገባል መዞሩ ሐዋርያት ከዕርገት በኋላ የጌታን ነገረ ሕማሙን ዞረው የማስተማራቸው ምሳሌ። አንድም በዕለተ ዐርብ አይሁድ ጌታን ሲቸነክሩት በቀኖት የፈሰሰውን ደሙን መላእክት በጽዋ ተቀብለው ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ረጭተውታልና የዚያ ምሳሌ ድርገት ሲመለስ እጅ መንሣት ሐዋርያት በዕርገት እጅ ነሥተው ለመቅረታቸው ምሳሌ ነው። ዲያቆኑም የጌታ ምሳሌ ነው፤ ነአኵቶ የንዑ ኀቤየ፤ ሥጋው ደሙ የምስሐ ደብረ ጽዮን ምሳሌ ነው።

Scanned by CamScanner

ዲ.ክ. ስብሐተ አግዚአብሔር ይነግር አፉየ።

ትርጓሜው እንዳለፈውነው።

ይ.ሕ. አቡነ ዘበሰማያት።

ትርጓሜው እንዳለፈው ነው፡

አኮ በሥሉ ፅዝል ዘይትበሃል።

ፅዝል በሚቀደስበት ጊዜ ሁሉ አሌፅለከ የሚባል አይደለም።

አላ በበዓላተ እግዚእነ ወበዓላተ እግዝእትነ ወበአሐዱ ሰንበት።

በጌታ በዘጠኙ በዓላት፤ በእመቤታች በዓላት፤ አሐዱ አሐዱ ፅዝልም ቢሆን በግፅዝም ቢሆን አሌፅለከ። በሌላው ቀን ፅዝልም ቢሆን ግፅዝም ቢሆን ስብሐተ እግዚአብሔር ይነግር አፉየ ማለት ይገባል። ድርገት ሲወርድ መውደቅ እጅ መንሣት ይገባል። ስለምን ቢሉ ቅዱሳት አንስት ከመቃብር ደርሰው ሲመለሱ ወተራክቦን እግዚእ ኢየሱስ በፍኖት ወይቤሎን በሐክን ይላል። ጌታ ከመንገድ አግኝታቸው እንዴት ሰነበታችሁ አላቸው። አኃዛ እገሪሁ ቀርባ ወሰገዳ ሎቱ ይላል። ከእግሩ ወድቀው ስግደውለታልና የዚያ ምሳሌ። ድርገት ወደ ምዕራብ መውረዱ ጌታ ወደ እዚህ ዓለም የመምጣቱ ምሳሌ፤ ወደ ምሥራቅ መመለሱ የዕርገቱ ምሳሌ። አንድም ወደ ምዕራብ መውረዱ ጌታ ፊቱን ወደ ምዕራብ መልሶ ለመሰቀሉ ምሳሌ እስመ ገጹ ለእግዚአብሔር መንገለ ምዕራብ ከመ ይነጽር ኵሉ ሕዝብ መንገለ ብርሃኑ ዘይሠርቅ እንዲል። ወደ ምሥራቅ መመለሱ የትንሣኤ አምሳል ነው። ከወጡም በኋላ ዲያቆን አንድ ጊዜ ዞሮ ይገባል መዞሩ ሐዋርያት ከዕርገት በኋላ የጌታን ነገረ ሕማሙን ዞረው የማስተማራቸው ምሳሌ። አንድም በዕለተ ዐርብ አይሁድ ጌታን ሲቸነክሩት በቀኖት የፈሰሰውን ደሙን መላእክት በጽዋ ተቀብለው ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ረጭተውታልና የዚያ ምሳሌ ድርገት ሲመለስ እጅ መንሣት ሐዋርያት በዕርገት እጅ ነሥተው ለመቅረታቸው ምሳሌ ነው። ዲያቆኑም የጌታ ምሳሌ ነው፤ ነአኵቶ የንዑ ኀቤየ፤ ሥጋው ደሙ የምስሐ ደብረ ጽዮን ምሳሌ ነው።

Scanned by CamScanner